## የዉዝፍ መዛግብት ሰበር ችሎት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 240468

ሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡---ሱልጣን አባተማም

ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ዘዉዲቱ ታደሰ

አመልካቾች፡-----1ኛ/ ወ/ሪት ሰላማዊት ላዕከ

2ኛ/ ወ/ሮ እሌኒ በስፋት

3ኛ/ ወ/ሮ አስናቀች ደርሶ

4ኛ/ አቶ ጌታቸዉ ወለላዉ

} ጠበቃ መስፍን ኃይሉ

ተጠሪዎች፡---1ኛ/የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባና ካብኔ ጉዳዮች ጽ/ቤት

2ኛ/የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ

} ዐ/ሕግ አለማየሁ ብርሃነ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠ

**ፍርድ**

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያስተናገደዉ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች እና ሌሎች 12 ሰዎች ከሳሾች በመሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ሆነዉ በተከራከሩበት ጉዳይ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ አጠር ባለ መለኩ ሲታይ፡- አመልካቾች በላፍቶ ክፍለ ከተማ እና ቦሌ ክፍለ ከተሞች በተለያዩ መኖሪያ ቤት ማህበራት ተደራጅተን በተሰጠን የግል ይዞታ ላይ ቤት ሰርተን ከ15 ዓመታት በላይ የያዝንና በ1997 ዓ.ም ላይን ማፕ ላይ የሚታይ ሲሆን በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት አግባብ ባለዉ አካል ሳይፈቀድ የተያዙ ቦታዎች ቢሆኑ እንኳን እንደሌሎቹ ዜጎች በእኩልነት መተስናገድ ሲገባን ተጠሪዎች ቃለ ጉባኤ በመያዝና ለሁሉም ክፍለ ከተሞች ሰርኩላር በማስተላለፍ በወንጀል ተጠያቂ የሆኑ አባላትና ቤተሰቦቻቸዉ ግንባታ ያረፈበትን ባዶ ቦታን እንዳይስተናገዱ እና ይዞታችን ወደ

መሬት ባንክ እንዲገቡ መወሰኑ በወንጀል ተጠያቂ የሆኑ ሰዎች ንብረት እንዲወረስ ፍርድ ባላረፈበትና ከወንጀል ፈፃሚዎች አልፎ በወንጀል ተጠያቂ የሆኑትን ቤተሰብ አባላቶች በመሆናችን ብቻ ይዞታችን እንዲወረስ  የሚፈቅድ ህግ፣ዉል ወይም መመሪያ  ሳይኖር ይዞታችን ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ መደረጉ ሕግን ያለተከተለ ነዉ ተብሎ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት እንድንስተናገድ እና ይዞታችንን እንዲያስረክቡን ይወሰንልን ሲሉ ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ያቀረቡት የመከላከያ መልስም ሲታይ አመልካቾች በተጭበረበረ መልኩ የህዝብና የመንግስት መሬት በመያዛቸዉ በሙስና ወንጀል ተከሰዉ ጥፋተኛ ተብለዉ የተቀጡ በመሆናቸዉ የወንጀል ፍሬ የሆነዉን ይዞታን በተመለከተ ተጠሪዎች በከተማ አስተዳደሩ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና በደንብ ቁጥር 49/2004 መሰረት የተሰጠዉን ስልጣን በመጠቀም አመልካቾች በሕጋዊ መንገድ ሳይደራጁ፣በማህበራት ማቋቋሚያ ስነ-ስርዓቱን ተከትሎ የተመሰረተ ማህበር ሳይኖር በሕገ ወጥ መንገድ ይዞታዎችን ይዘዉ በመገኘታቸዉ እና የወንጀል ፍሬ በመሆናቸዉ እንዲወረሱ መደረጉ በአግባቡ ስለሆነ የአመልካቾች ክስ ዉድቅ ይደረግልን ሲሉ መልስ ሰጥቷል፡፡

ግራ ቀኙን በዚህ መልኩ ያከራከረዉ የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች የክሱ መነሻ የሆነዉን ይዞታ በማህበር ተደራጅተዉ ከ15 አመታት በላይ የኖሩበት  ከመሆኑ አኳያ የወንጀል መዝገቡን አስቀርቤ ስመለከተዉ ከአመልካቾች መካከል 2  እና የአመልካቾች አባት ብቻ በወንጀሉ ጥፋተኛ የተባሉ ሲሆን ሌሎቹን አመልካቾች በተመለከተ የተላለፈ የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ አልቀረበም በወንጀል ችሎቱም እንዲወረስ የሚል ዉሳኔ አልተሰጠም እንዲሁም የዜጎች ይዞታ ሊወረስ የሚገባዉ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ወይም በሕግ አግባብ በመሆን ሲገባዉ ሌሎች ሕግ ወጥ ማህበራት በመመሪያዉ እንዲስተናገዱ እየተደረገ ሳለ መመሪያዉ በወንጀል የተቀጣና ያልተቀጣ በሚል መለያ መስፈርት ባላስቀመጠበት ሁኔታ በወንጀል የተቀጡትን ይዞታቸዉ ወደ መሬት ባንክ ይመለስ በማለት መወሰኑ ሕገ መንግስታዊ የዜጎችን እኩልነት መርህን  የሚፃረር በመሆኑ የአመልካቾች ይዞታ ወደ መሬት ባንክ ይግባ ሲሉ ተጠሪዎች የወሰኑት ዉሳኔ ተገቢ አይደለም በማለትና አመልካቾች የያዙትን ይዞታ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት ተገቢዉ የይዞታ መንስተንግዶ ሊስተናገዱ ይገባል ሲል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በዉሳኔዉ ቅሬታ አድሮባቸዉ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዉ ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉበት መዛግብት ላይ ይዞታዉን በተመለከተ የተላለፈ ዉሳኔ ባይኖርም ተጠሪዎች በመመሪያዉ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይዞታዉን በምን መልኩ እንደተያዘ በማጣራትና ሰነዶቸን መርምሮ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚችል ስለሆነ አመልካቾች ይዞታዉን በተመለከተ በወንጀል መዝገቡ ላይ ዉሳኔ አልተሰጠም በማለት ከሚከራከሩ በቀር ይዞታዉን በምን መልኩ እንዳገኙ ማስረጃዎችን በማቅረብ ባልተከራከሩበት ሁኔታ በወንጀል መዝገብ ላይ ይዞታዉ ይወረስ የሚል ዉሳኔ አልተሰጠም በሚል ምክንያት ብቻ ይዞታዉን ተጠሪዎች ወደ መሬት ባንክ ማስገባት የለበትም  ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት አለበት በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር ይዞታዉ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ በተጠሪዎች የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ሲል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በቀን 9/5/2015 ዓ.ም በተፃፈ ለዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጭሩ፡- አመልካቾች ከ15 አመታት በላይ በማህበር ተደራጅተን የያዝነዉ ይዞታ ላይ የተለያዩ ንብረቶች አፍርተን መብራት ዉሃ አስገብተን ይህን የምንኖርበትን ይዞታ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት አገልግሎት እንዲሰጠን

ስንጠይቅ መስተንግዶ ሊሰጠን እንደማይገባ እና የአዲስ አበባ ካብኔ በቃለ ጉባኤ ዉሳኔ ይዞታዉ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የተወሰነዉ ዉሳኔ ያለ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሲሆን በአንድ ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉ ግለሰቦች ቤተሰብ በመሆን ብቻዉን ንብረትን ለማስወረስ ዉጤት የሌለዉ ከመሆኑም ባለፈ በሕግ በተቀመጠዉ የወንጀል ፍሬ ተብሎ ይዞታዉ እንዲወረስ ዉሳኔ ሳይኖር እና የመመሪያ ቁጥር 18 /2006 አንቀጽ 14 ላይ ከማህበራት ጋር በተያያዘ በግልፅ ሊወረስ ወይም ወደ መሬት ባንክ ሊገባ የሚችል የማህበራት ይዞታ በፍርድ ቤት የተወሰነ ብቻ ከሆነ መሆኑን ደንግጎ ሳለ ያለ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዞታችን እንዲወረስ መወሰኑ ስህተት ነዉ እንዲሁም ግራ ቀኙ በአከራካሪዉ ጉዳይ ላይ በተጠሪዎች በቃለ- ጉባኤ የተሰጠዉ ዉሳኔ እና የመመሪያ ቁጥር 18/2006 ክርክር ባስነሳዉ ይዞታ ላይ ልዩነት አላቸዉ ካሉ ተፈፃሚ የሚሆነዉ የትኛዉ ነዉ የሚለዉ ካሉት ሁለቱ አማራጮች የአመልካቾች ይዞታ ወደ መሬት ባንክ የተላለፈበት አግባብነት በተመለከተ ተገቢዉ ጭብጥ ተይዞ ሳይወሰን መቅረቱ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ በወንጀል ተጠያቂ የሆኑ ማህበራት አባለት የነበሩና በወንጀል ተጠያቂ የነበሩ ግለሰቦች በዉሳኔዉ በመቋወም በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት ለመስተናገድ ያቀረቡት የፍትሐብሔር ክስ መብት አስገኝቶላቸዉ ዉሳኔዉ እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 159201 ላይ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ የአመልካቾች ክስ ዉድቅ መደረጉ የእኩልነት መርህን የጣሰ እና በዜጎች መካከል ልዩነት የፈጠረ በመሆኑ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይታረምልን ሲሉ ጠይቋል፡፡

አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መነሻ ተደርጎ አመልካቾች የክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ ይዘዉ ይገለገሉበት የነበረ ስለመሆናቸዉ በተገለፀበትና ይዞታዉም የወንጀል ፍሬ ስለመሆኑ ዉሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ በመመሪያዉ ልትስተናገዱ አይገባም በሚል ይዞታዉ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የተወሰነበት አግባብነት ከመመሪያ ቁጥር 18/2006 አኳያ ለማጣራት ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡

ተጠሪዎች የሰጡት መልስም አጠር ባለ መልኩ ሲቀርብ ፡- የሰበር አመልካቾች አከራካሪዉን መሬት የያዙት ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት እና ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ማህበራትን በማደራጀት የያዙ መሆናቸዉ ተረጋገጦ በዚህም በወንጀል ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑ በዚህ ይዞታ ላይ ተጠሪዎች ያላቸዉን ስልጣን በተመለከተ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 አንቀጽ 12(12) ላይ ተደገገዉ በማህበር በማደራጀት የተያዘ ይዞታም ሆነ ከይዞታዉ አመጣጥ ህጋዊነት ጋር በተያያዘ ጉዳያቸዉ ስልጣን ባለዉ አካል ዉሳኔ ያገኘ ወይም በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲታዩ የተላለፉ ይዞታዎችን በተመለከተ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትን ችግር ለመፍታት ባዘጋጀዉ መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 4 (4-6) መሰረት ካብኔዉ እያንዳንዱን ማህበራት ጉዳይ እየመረመረ በቀጣይ ዉሳኔ እንደ ሚሰጥበት ስልጣን የተሰጠዉ ስለሆነ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ለካቢኔዉ በተሰጠዉ ህጋዊ ስልጣን መሰረት ተጣርቶ የተወሰነዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ በመባሉ ትክክል ነዉ የሚል ክርክር ያቀረቡ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ አመልካቾች በክሱ መነሻ የሆነዉን ይዞታ ያገኙበት መንገድ በህግ ወጥ ስለመሆኑ እንዲሁም

በጉዳዩ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለዉ የተቀጡበት ሲሆን ይህ ደግሞ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 66943 በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ላይ አንድ ሰዉ የወንጀል ክስ ቀርቦበት የጥፋተኝነት ዉሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘዉን ንብረት በመንግስት መወረስ

እንዳለበት የሚገልፅ ስለሆነ ከዚህ አንፃር ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ያለበት አይደለም ተብሎ እንዲፀናላቸዉ ጠይቋል፡፡ የሰበር አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸዉን የሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት አድርጎ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለ ወይስ የለም የሚለዉን ጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል ፡፡

የክሱ መነሻ የሆነዉን ይዞታ አመልካቾች የያዙት በህገ ወጥ መልኩ መሆኑን አከራካሪ ጉዳይ አይደለም የአመልካቾች የሰበር ቅሬታ ይዞታዉን በሕገ ወጥ መልኩም ቢያዝም ከይዞታዉ ጋር በተየያዘ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉም ቢሆንም በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት በይዞታዉ ላለመስተናገድ የሚያግደን ነገር የለም እንዲሁም በወንጀል መዝገቡ ላይ የክሱ መነሻ የሆነዉ ይዞታ ይወረስ የሚል ዉሳኔ ስለሌለ ይገባናል የሚሉ ሲሆን ተጠሪዎች በኩል ደግሞ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 አንቀጽ 12(12) ላይ ተደገገዉ በማህበር በማደራጀት የተያዘ ይዞታም ሆነ ከይዞታዉ አመጣጥ ህጋዊነት ጋር በተያያዘ ጉዳያቸዉ ስልጣን ባለዉ አካል ዉሳኔ ያገኘ ወይም በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲታዩ የተላለፉ ይዞታዎችን በተመለከተ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትን ችግር ለመፍታት ባዘጋጀዉ መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 4 (4-6) መሰረት ካብኔዉ እያንዳንዱን ማህበራት ጉዳይ እየመረመረ በቀጣይ ዉሳኔ እንደ ሚሰጥበት ስልጣን የተሰጠዉ ስለሆነ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ለካቢኔዉ በተሰጠዉ ህጋዊ ስልጣን መሰረት ተጣርቶ የተወሰነ ስለሆነ ተገቢነት አለዉ የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የክሱ መነሻ የሆነዉን ይዞታ አመልካቾች ሕገ ወጥ ማህበር በማቋቋም የያዙ ስለመሆኑም ሆነ በዚህ ድርጊታቸዉ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለዉ የቅጣት ዉሳኔ የተላለፈባቸዉ ስለመሆኑ አይካድም አመልካቾች አሁንም እየተከራከሩ ያሉት መሬቱን በሕገ ወጥ መንገድ ብንይዝም እንዲሁም በወንጀል ጥፋተኛ የተባልንም ቢሆንም መሬቱ እንዲወረስ በፍርድ ቤት ዉሳኔ ያልተሰጠ በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት ልንስተናገድ ይገባል የሚለዉ ክርክር ስንመረምረዉ መሬት እና መሬት ነክ ጉዳዩችን የመመዝገብ እና የመቆጣጠር ስልጣን የተሰጣቸዉ የአስተዳደር አካሉ ስለመሆኑ አጣያያቂ አይደለም ይህም ስልጣናቸዉ የአዲስ አበባ ከተማ የሚያስተዳደረዉን ይዞታ በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና ደንብ ቁጥር 49/2004 ላይ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

በክሱ መነሻ በሆነዉን የማህበራትን መሬት ጉዳይ በተመለከተ የመመሪያ ቁጥር 18/2006 አንቀጽ 12 እና መመሪያ ቁጥር 7/2003 መሰረት በማህበር ተደራጅተዉ የተያዙ ይዞታዎችን ሆነ ከይዞታዉ አመጣጥ ሕጋዊነት ጋር በተያያዘ ጉዳያቸዉ አይቶ የመወሰን ስልጣን ለተጠሪዎች የተሰጠ በመሆኑ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አመልካቾች ይዞታዉን ያገኙበት ሁኔታ አመልካቾች በህጋዊ መንገድ ሳይደራጁ፣ የማህበራት ማቋቋሚያ ስነ-

ስርአቱን ተከትሎ የተመሰረተ ማህበር ሳይኖራቸዉ፤ ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅተዉ፤ ሀሰተኛ ማህበር አቋቁመዉ የያዙት መሆኑን እና በወንጀልም ጥፋተኛ የሆኑበት መሆኑን ካብኔዉ በተሰጠዉ ስልጣን አጣርቶ እና መርምሮ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ሲሉ የሰጡት ዉሳኔ ተገቢነት ያለዉ ተብሏል፡፡

ከዚህ ሌላ አመልካቾች የጠቀሱት የሰበር በአጣሪ ችሎት ዉሳኔ ይህ ችሎት የሚገደድበት የህግ አግባብ ስለሌለ ከዚህ አኳያ የቀረበዉን ክርክራቸዉ ተቀባይነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፌ/ከ/ፍ/ቤቱ ለአመልካቾች ይዞታዉ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት ሕጋዊ እንዲሆንላቸዉ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና ደንብ ቁጥር 49/2004 በተሰጣቸዉ ስልጣን በመጠቀም አመልካቾች በህጋዊ መንገድ ሳይደራጁ፣ የማህበራት ማቋቋሚያ ስነ-ስርአቱን ተከትሎ የተመሰረተ ማህበር ሳይኖራቸዉ፤ ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅተዉ፤ ሀሰተኛ ማህበር አቋቁመዉ የያዙት መሆኑን እና በወንጀል ፍሬ ይዞታን በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት ሕጋዊ እንዲሆንላቸዉ ያቀረቡትን ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ መሬቱን ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ መደረጉ በአግባቡ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም ፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ዉሳኔ**

1/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባን ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 209927 ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 220865 ግንቦት 09 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ተብሎ በፍ/ብ/ህ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2/ ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ ወገኖች ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

**ማስታወሻ፡** - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ የግ ለግልም!